# ቀንድ አውጣ



ሰተት ብሎ ወጥቶ ጥምዝምዝ ቤቱን
ተሸክሞ ሲያዘግም ገልጦ ብልቱን
ቀንዱንም ገትሮ ዕራቁቱን ሲሄድ
ቀንድ-አውጣ ባለጌ ነው ወይንስ ዕብድ?
ሞኝ አይደል ብልጥ ነው ነገር ግን ብልሓቱ
ከቀንዱ አይደለም ተንኰሉ፣ ብልጠቱ።

አራት ቀንዶች አሉት የላይና ታች
ለመውጋትስ ቀርቶ ለምንም 'ማይመች
ለጌጥ ተሸክሞት ሁለት የቀንድ መንታ
ኮሰስ ብሎ ሲሄድ፣ ሲያዘግም፣ ሲያመነታ
ቀንድ አለኝ ብሎ ነው ያን ለስላሳ ስጋ
አይጎስም፣ አይጐሽም፣ አይመታ፣ አይዋጋ
ያወዛውዘዋል እንደ ማራገብያ
ሊያጌጥበት ይሆን ወይስ ማስፈራሪያ?



ብልጠቱን፣ ብልሓቱን ስሙኝ ላስረዳችሁ
ዕርቃኑን ቢወጣም ሞኝ አይምሰላችሁ
ደግሞም ባለጌ ነው፣ ዕብድ ነው ካላችሁ
የቀንድ አውጣን ብልጠት እኔ ልንገራችሁ
ሲሻው ዕራቁቱን ይላል ብቅ-ጥልቅ
ጠላት ሲመጣበት ቤቱ ገብቶ ድብቅ...



ሲጓዝ፣ ሲያመነታ ኮሰስም እያለ
ብልጥ ነው ቀንድ-አውጣ ሞኝ እየመሰለ
ብልጠቱ፣ ተንኰሉ፣ ብልሓቱና ጉዱ
ከጥምዝዝ ቤቱ እንጂ አይደለም ከቀንዱ፤
በጋ ሆነ ክረምት መካሪ ሳይኖረው
ዝናብ ሆነ ፀሓይ ምንም ሳይቸግረው
ከሳሩ፣ ከአፈሩ፣ ከጉሬው፣ ከጥሻው
ኦረ እንደምን ቻለው ኮስማናው ትከሻው!
ቤቱን ተሸክሞ ያዘግማል እንዳሻው...



ኦረ በምን ምክንያት ይሆን የጀመርከው፣
ቤትህን ተሸክመህ ለመሄድ የቻልከው?
ንገረኝ ቀንድ-አውጣ እንዴትስ ለመድከው?
መባረክ እንዲህ ነው፣ ምንኛ ታድለህ!
ልብስም ሳትፈልግ ዕብድና ሞኝ መስለህ
ኮተትህን፣ ጓዝህን እንዳለ ጠቅልለህ፣
ወደ ፈለግክበት ቀንተህ ታዘግማለህ።
ጉልበትስ በኖረኝ ምነው በታደልኩት
ቀንድ-አውጣ ባረገኝ፣ በተገላገልኩት!

ማደርያየን ይዤ ቤት ኪራይ ሳልከፍል
ከማያልቀው ዕዳ እንድገላገል!
የትም ዞሬ-ዞሬ፣ ከየትም አገር
ክረምት ሆነ በጋ፣ ብርድና ሃሩር
ከፈቀደኝ ሄጄ፣ ከመሸበት ላድር…
እስቲ ምን በሠራሁ፣ ኦረ በምን ሓጢአት
መረሮኛል! መረሮኛል! የኪራዩ መብዛት
እንደ ሴት ልጅ ዕዳ በየወሩ መድማት!

ሾርባ፣ ምንትሴ፣ ቅብጥርሴ እያሉ
ፈረንሳዮች ለጉድ ቀንድ-አውጣ ይበላሉ!
እኔንስ ያማረኝ አይደለም መብላቱ
ቤት ኖሮኝ በሕጉ፣ በስነ-ሥርዓቱ
ተሸክሜ እየዞርኩ በቀን፣ በሌሊቱ
እንዳሻኝ ገብቼ፣ እንዳሻኝ መውጣቱ…
በታደልኩትና ባረገኝ ቀንድ-አውጣ
ሽፍንፍን ብዬ፣ ዕርቃኔም ብወጣ
ሳልባል ቅሌታም፣ ሳልባል ቀልብ-አጣ
አንዷን ቆንጆ ይዤ ሸጊት፣ ቀበጥባጣ
በሞቀው ቤቴ ውስጥ ዓርፋ፣ ተቀምጣ
"ነዪ ቶሎ!" ስላት ወደኔ እምትመጣ…

ምንም ኪራይ ሳልከፍል የትም እያደርኩ
ጉልበቴ እንደቻለው ሁሌ እያዘገምኩ
ወዳጄን ታቅፌ እየተደሰትኩ
ጠላትም ሲመጣ እየተደበቅኩ
ቤቴን ተሸክሜ የትም እየኖርኩ
ለፓስፖርት ሳላስብ ዓለምን በዞርኩ!

ግ/ኢ. ጐርፉ።



